# ረመዷን የመንፈሳውያን ቅዱስ ጊዜ እንጂ የቀድሞው ቅንጅት ስብርባሪዎች እና የደርጉ ሥርአት የሳንሱር ኦፊሰሮች አይደለችም!!

# (ክፍል 2)

**ሚስባህ**

ትውስታ! የመጣጥፌ መነሻ "ረመዷንን ጠርጥሮ ምርጫን በጓሮ" በሚል ርዕስ ፍትህ ጋዜጣ በሴኔ 8 አቅሟ ያስነበበችን እና በአቶ ሁሴን ከድር የተፃፈው መጣጥፍ መሆኑን በክፍል አንድ ላይ ገልጫለሁ፡፡ በዚህ ጽሁፌ ደግሞ በዋናነት አቶ ሁሴን ከድር የተባሉትን ግለሰብ እንደ አቶ ሁሴን ካቀረቡት መጣጥፍ አንፃር የፈተሸኩኝና ያነጠርኩኝ ሲሆን ከመጣጥፉ ላይ አቶ ሁሴን ከድር የቀድሞው የጦቢያ መጽሄት ጋዜጠኛ መሆናቸው በተገለጸው መሰረት በዚህ ሁለተኛ ክፍል መጣጥፌ ግለሰቡን እንደቀደሞው የጦቢያ መጽሄት ጋዜጠኛ ካቀረቡት መጣጥፍ አንፃር የምቃኝ እንደሆነ በይደር ባቆየሁት መሰረት የቀድሞው የጦቢያ መጽሄት ጋዜጠኛ ሁሴን ከድር እና "ረመዳንን ጠርጥሮ ምርጫን በጓሮ" ዛሬ አብረውን ይቆያሉ ማለት ነው፡፡

ላለፉት 13 አመታት በጋዜጠኝነት ሙያ እንዳገለገለ በመጣጥፉ ላይ የሚነግረን "ጋዜጠኛ" ሁሴን ከድር የተለያዩ ምሁራንን በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንዳነጋገረ በመግለጽ በሙያው "የካበተ" ልምድ እንዳለው ወይም በመጣጥፉ ላይ ስለዘረዘራቸው ጉዳዮች ምንም ጥርጣሬ እንዳይገባን የፈለገ የሚመስል መልእክት አስተላልፏል፡፡ ነገር ግን እንኳን የካበተ የጋዜጠኝነት ሙያ ያለው፣ እንኳንስ በርካታ ምሁራንን ያነጋገረና ለ13 ዓመታት በሙያው ውስጥ ያለፈ ጋዜጠኛ ቀርቶ ጀማሪ ጋዜጠኛ እንኳ ሳይሆን ፊደል የቆጠረ ሁሉ ይሳሳታል ብለን በማንጠብቀው ደረጃ የቀድሞው የጦቢያ ጋዜጠኛ ሁሴን ከድር እዚያና እዚህ የረገጠ የብእር ውስልትና በግልጽ የታየበት መጣጥፉን እመኑኝ ጥርጣሬ አይግባችሁ ሲል መሞገቱ ግራ የሚያጋባ ነው፡፡ በኔ በኩል ስህተቱ ሆን ተብሎ የተደረገና የቀድሞው ቅንጅት ስብርባሪ ግለሰቦች የሆኑትን ሁሉ ለመሆን የተደረገ ሙከራ መሆኑን ያመላከተኝ መጣጥፍ በመሆኑ፡፡

ማሳያዎች አቀርባለሁ፦ ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ሊያስማማ የሚችል ህገ መንግስት አርቅቆ ተግባራዊ ማድረግ ከጀመረ ወዲህ ሙስሊሙ ህብረተሰብ ህገመንግስቱ የሰጠውን ነፃነት መጠቀም ጀምሯል በማለት ምጡን የተገላገለው "ጋዜጠኛ" ሁሴን በአገራችን የእምነት ነፃነት ስለመረጋገጡና ሙስሊሙ ህብረተሰብ እምነቱን በነፃነት ማራመድ መቻሉን "ሙስሊሙ ህብረተሰብ ባለፉት 20 ዓመታት የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣቱ አይካድም፡፡ ይህም የሆነው መንግስት በፈጠረው ምቹ ሁኔታ ነው፡፡" በማለት ያረጋግጣል፡፡

ከዚህ በኋላ ነው እንግዲህ ሊያውም እስከ መጣጥፉ መደመደሚያ እንኳን በአቋሙ መዝለቅ እንደማይችል እያወቀው ብእሩ መወስለት የጀመረው፡፡ መንግስት በፈጠረው ምቹ ሁኔታ ሙስሊሙ እምነቱን በነፃነት ማራመድና የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣቱን ቀደም ብሎ የነገረን "ጋዜጠኛ" ሁሴን መልሶ "መንግስት ለክፉ የተመኘው ህዝበ ሙስሊም በተቃራኒው በፍቅርና በወዳጅነት መንፈስ በመሰባሰብ አንድ መሆን ጀምሯል፡፡" ይለናል፡፡ ሃሳቡ የተቃረነና እርስ በርሱ የተጣረሰ መሆኑ፤ በውስጡ ተንኮልና ሴራ የሞላበት መሆኑን ትተን መንግስት ለክፉ የተመኘው "ህዝበ ሙስሊም አንድ ሆኗል" ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን እንመልከት፦

እስልምና ዓለም አቀፍ እምነት  እንደመሆኑ ከአስተምህሮ አንፃር በውስጡ የተለያዩ ስያሜዎች ያላቸው ነገር ግን እስልምና ቁርዓን የጋራቸውና ገዢ ሰነዳቸው እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በዚህ መሰረት "ጋዜጠኛው" ሁሴን በአገራችን የሚገኙ የሱፊ ሱኒ ሙስሊሞች፣ አክራሪ የሆኑት ወሃቢዎቹና አልሀበሾቹ ሁሉም አንድ ሆነዋል እያለን ነው፡፡ አልሀበሹም (የሱኒ ሱፊውም) አክራሪ ወሃቢዩም አንድ ሆነናል የሚለን "ጋዜጠኛ" ሁሴን መንግሥት በዚህ በአንድነታችን በግኖ ሊነጣጥለን የተለያዩ ስያሜዎች በመለጠፍ እየሰራብን ነው ብሎ ከላይ ስለ እስልምና የእምነት ነፃነት መከበር አሰተዋጽኦው የጎላ ነው ያለውን እና ያወደሰውን መንግስትና ህገመንግስት መልሶ በመኮነን ቁልቁል ይንሸራተታል፡፡

በነብዩ መሃመድ ዘመን ሃይማኖታዊ መሪዎች የሚመረጡት በመስጅድ ነው ብሎ በዚሁ መጣጥፍ የሚከራከረው "ጋዜጠኛ" ሁሴን  አሁንም ምርጫ መከናወን ያለበት በመስጅዶች ነው ሲል ባህልና ልማድ መለውጥ እንደሌለበት ይሞግታል፡፡ ባለፈው መጣጥፌ ለመጠቆም እንደሞከርኩት ዛሬ ከሃገራችን ህዝቦች ከ33 በመቶ በላይ የሚሆነው የእስልምና እምነት ተከታይ በሆነበት ሁኔታ፤ ምንም እንኳን በርካታ መስጅዶች ባለፉት 20 ዓመታት የታነፁ ቢሆንም የሙስሊሙን ህብረተሰብ አሰፋፈር የሚያማክሉ (አንዳንዱ ጋር ከአማኙ ቁጥር በላይ መብዛታቸው ፤ አንዳንዱ ጋር ደግሞ ጭርሱን የሌሉበት እና  በርቀት የሚገኙ) ከመሆኑ አንፃርና ምርጫው የአማኙን ሁሉ ውክልና ማረጋገጥ ስላለበት በወረዳ ደረጃ መከናወኑ ትክክል ስለመሆኑ፤ ይህ አሰራር ደግሞ አምናና ካቻምናም እንደነበር ገልጫለሁ፡፡

የነብዩ መሃመድ ዘመን የምርጫ አካሄድ መለወጥ የለበትም ሲል የተከራከረው ጋዜጠኛ ሁሴን ዝቅ ብሎ "በፊት የነበሩት ባህሎች፣ ወጎች፣ ደንቦችና ስርዓቶች ዛሬ እየተለወጡና እየተሻሻሉ በአዳዲስ እየተተኩ መጥተዋል፡፡ ሌላው ቀርቶ አልባሳት በዘመኑ ተለውጠዋል፣ የፀጉር አበጣጠር ስልት፤ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የዘይቤ፣ የስልታዊ አነጋገር፣ ከዘመንና ከለውጥ ጋር ከእድገትና ከእውቀት ጋር ይለወጣል" በማለት የቀድሞ ስርዓት መለወጥ የለበትም ሲል ከላይ የሞገተለትን ሃሳብ ከገደል ይዶለዋል፡፡

የ"ጋዜጠኛው" እርስ በርሱ የተገማመደና ውሉ የጠፋ ሃሳብ አሁንም እንደቀጠለ ነው፡፡ መንግስት በእስልምና እምነት መሃል ጣልቃ ገብቶ አንዱን አስተምህሮ "መጤ" ሌላውን "ነባር" የሚል ታፔላ መለጠፉ ተገቢ አይደለም፡፡ አባባሉ የከፋፋዮችና የአምባገነኖች ነው ሲለን የነበረው "ጋዜጠኛ" በመቀጠል "በአሁኑ ጊዜ በአንድ ወረዳ ውስጥ ያሉ ዜጎች የሚተዋወቁ አይደሉም፡፡ ማን አዲስ ይሁን ማን ነባር፣ የቱ የወረዳው ነዋሪ ይሁን የትኛው መጤ የወረዳው ሰዎች አያውቁም፤ ለመሆኑ መንግስት እንደሚፈልገው ምርጫው በወረዳ ከተካሄደ ሙስሊሙ መሪ መረጠ ሊባል ነው? ቀድሞ ነገር መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ምን ጥልቅ አደረገውና ነው በፌዴራል ጉዳይ ቢሮ አማካይነት ምርጫውን የሚያካሂድልን" በማለት በእርሱ አገላለጽ የመንግስትን የከፋፋይነትና አምባገነንነት ባህሪ ይደግማል፡፡

"የሙስሊሙ ጥያቄ ተመልሷልን?" ሲል ባሰፈረው ንዑስ ርእስ ስር ሙስሊሙ ቢያንስ ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎችን ለመንግስት ማቅረቡን የሚያረጋግጠው" "ጋዜጠኛ" መልሶ ለመሆኑ መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ምን ጥልቅ አደረገውና ነው? ሲል መጠየቁ የእብደት ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም በህገመንግስቱ እንደተገለጸው መንግስት "በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም" በሙስሊሙ ህብረተሰብ ለመንግስት የቀረበው ጥያቄ ህገመንግስቱን በራሱ የሚፃረር ሆኖ ከነበረ ለምንስ መጀመሪያውኑ አወልያው ጥያቄ አቀረበ? ጥያቄያቸው ህገመንግስቱን የሚፃረር ከሆነ ምንም እንኳን ያኛው ስለተሳሳተ መንግስት መሳሳት አለበት ባይባልም ጥያቄው ህገመንግስቱን የሚፃረር ከሆነ በነጋዜጠኛ ሁሴን ከድር ተጠየቀ መሰረት መንግስት ጣልቃ እንዲገባ መጀመሪያውኑ በሩን የከፈተው አወልያው ነው ማለት ነው፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ የአወልያው ኮሚቴ ሊረከበው የቋመጠለትን መጅሊስ እንደማያገኘው እና በአንፃሩ ደግሞ ምዕመኑ የመረጠው ወኪል በቦታው ላይ ሊሰየም እንደሚችል ቁርጡን እያወቀ የመጣው የጋዜጠኛ ሁሴን ከድር ስብስብ ቀድሞ ነገር መንግስት ምን ጥልቅ አደረገውና ቢለን እራሱ ገርፎ የሎኘውን ጅራፍ  አይነት ነገር  ነው የሚሆነው፡፡ በእርግጥ መንግሥትን የሚመለከተው ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱን ተከትሎ የዜጎችን መብት በእኩልነት ከማስከበርና የህብረተሰቡን ደህንነት ከማስጠበቅ እንጅ፤ በሃይማኖታዊ ሥርአቱ ጉዳይ ውስጥ ገብቶ ምእመኑን ይህን አድርግ፤ ያንን አታድርግ፤ እገሌን ተከተል ወዘተ በሚል እንዳልሆነ በግልጽ ይታወቃል፡፡

ከላይ የነካኳኳቸው የ"ጋዜጠኛው" መሰረታዊ ግድፈቶችና ድብቅ አጀንዳዎች እንደተጠበቁ ሆነው የ"ጋዜጠኛው" ከንቱ መባዘንና ለማደናቆር መሞከር ዋነኛ ምንጭ ግን ከዚሁ ከ"ቀድሞ የጦቢያ መፅሄት ጋዜጠኛ" ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የመጣ ነው ብዬ አፌን ሞልቼ ለመናገር እደፍራለሁ፡፡

"ጋዜጠኛ" ሁሴን ከድር ጋዜጠኛ ነበርኩበት የሚለን ጦቢያ መፅሄትን እናስታውስ፦

የፕሬስ ነፃነት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በተረጋገጠበትና ህገ መንግስታዊ ዋስትና ባገኘበት ማግስት እንደአሸን ከፈሉት ውስጥ በስርጭት ረገድ የተሻለ የነበረው የጦቢያ መጽሄት መስራች አሳታሚና ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ሙሉጌታ ሉሌ ይባላል፡፡

ጋዜጣና ጋዜጠኝነት ፣ ሚዲያና ጋዜጠኝነት ከተባለ ፣በደርጉ ሥርዓት በነበሩት የኢሠፓ ሚዲያዎችና ጋዜጦች ላይ ከፍተኛ ሚና ከነበራቸውና
የማይለቅ አሻራቸውን ካሳረፉት የሥነፅሁፍና የጋዜጠኝነት ሰዎች አንፃር ሙሉጌታ ሉሌ ግንባር ቀደሙ ነው፡፡ ሙሉጌታ ሉሌ የኢሠፓው ሰርቶ አደር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ከመሆን ጀምሮ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ በነበረው ከፍተኛ ስልጣን የዘመኑ ከፍተኛ የሳንሱር ኦፊሰር ሆኖም ሰርቷል፡፡

ታማኝ በመሆኑ እንደሎሎቹ ባልደረቦቹ በኮሌኔል መንግስቱ ሃይለማርያም ምንም ጉዳት ሳይገጥመው እሰከ 1983 የኢሰፓ ህዝብ ግኑኝነትና የፕሮፓጋንዳ ስራዎችን ሲመራ የነበረው ሙሉጌታ ሳይታሰብ የመጣውን ለውጥ ባለማመን "የጦር ገባ ጦር ወጣ "የቅጥፈት ፕሮፓጋንዳውን ጦቢያ የተባለች መጽሄት በማቋቋም እልሁንና ቁጭቱን ሲተነፍስ ከረመ፡፡

በጋዜጠኝነት ስም የተቋቋሙትና በከሰሩ ፖለቲከኞች ቁጥጥር ስር የነበሩት ጋዜጦች ቀስ በቀስ እንደጉም እየተነኑ ሲጠፉ ከፊሉ ጋዜጠኛ ፍልሰትን ሲመርጥ ገሚሱ ደግሞ የሃይማኖት ተቋማትንጨምሮ ባገኘው ስርቻ ሁሉ ሰርጎ በመግባት አሁንም ድረስ ምኞቱን ለማሳካት የተራራ ላይ ግዙፍ ቋጥኝ በጣቴ ካልፈነቀልኩ ሲል ይታያል፡፡

የጦቢያው አሳታሚ ሙሉጌታ ሉሌ ከፈለሱት የከሰሩ ፖለቲከኞች ውስጥ አንዱ ሲሆን አሁን አሸባሪ በሆነው ግንቦት 7 እና በከሰሩ ዲያስፖራ ፖለቲከኞች የተቋቋመው የኢሳት ድረገጽ የቦርድ አባል በመሆን የሽብር ፖለቲካ ፕሮፓጋንዳውን በመምራት ላይ እና እንደ አበበ ገላው የመሰሉ ጥገኞችን በመቆጣጠር ላይ ይገኛል፡፡

በሌላ በኩል የጦቢያው ባልደረባ የነበረው "ጋዜጠኛ" ሁሴን ከድር ደግሞ ሀገር ውስጥ እንደቀሩት የከሰሩ ባልደረቦቹ ሁሉ እሱም የሃይማኖት ካባ በመደረብ በከሰረው ቅንጅት ለተቋቋመው የግንቦት 7 የጥፋት ድምጽ ማሰሚያ የከበሮ መምቻ ሆነና አረፈው፡፡ ለዚህም ሌላውን እንኳ ብንተውለት በዚህቺው “ረመዷንን ጠርጥሮ ምርጫን በጓሮ” በምትለው ለረመዳን አመጽ በተመኘባት መጣጥፉ አቋሙን በግልጽ አረጋግጦልናል፡፡

የቀድሞው ቅንጅት ስብርባሪዎችና የደርጉ መንግስት የሳንሱር ኦፊሰሮች የፕሬስ ነፃነት በተረጋገጠ ማግስት ያኙትን አጋጣሚ ተጠቅመው ስርዓቱን ለመጣል የነበራቸውን ምኞት ዛሬ ደግሞ በሃይማኖት ሽፋን ምን እያደረጉ እንደሆነ በተለይም የሙስሊም ስም ያላቸው የኑፋቄ ፖለቲከኞች

ስርዓቱን ለመጣል ይህን የአወልያ ጥያቄ እንደምቹ አጋጣሚ ለመጠቀም በመውተርተር ላይ ስለመሆናቸው ማሳያ ከሆነን የቀድሞው የጦቢያ መጽሄት ጋዜጠኛ በተጫማሪ ሌላም ማሳያ ማቅረብ ይቻላል፡፡

ልክ እንደ ጦቢያ መጽሄት ስርዓቱን ለመጣል ይታገሉ ከነበሩት የግል ጋዜጦች መካከል "የአፍሪካ ቀንድ" የምትባለዋን ጋዜጣ እናስታውሳለን፡፡ የዚህቿው የከሰሩ ፖለቲከኞች እና የኢሰፓ ርዝራዦች የሆኑ ዓምደኞች መነኻሪያ የሆነችው የአፍሪካ ቀንድ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የነበረው ደግሞ አደም ካሚል የተባለ ግለሰብ መሆኑ አይዘነጋም፡፡

ታዲያ አሁን አደም ካሚል የትነው ያለው? ለምትሉ ልክ እንደ ሙሉጌታ ሉሌ ወደ ኢሳት መጠጋት፣ ልክ እንደሁሴን ክድር የሙስሊሞች ጋዜጣ አምደኝነት መቀላቀል ሁሉ አደም ካሚል ደግሞ የአወልያው ኮሚቴ አባል በመሆን አክራሪነትን በማቀንቀን ስርዓቱን በእጅ አዙር ለመጣልና ምኞቱን ለማሳካት እየጣረ ነው እላችኋለሁ፡፡

መንግስት የዕምነት ነጻነትን በማስጠበቅ ረገድ ያለውን ጽኑ  አቋምና በዚህም የሙስሊሙ መብት በሚገባ ስለመከበሩ እየመሰከሩ፣ ህገመንግስቱ ያረጋገጠውን ነፃነት እያወደሱና ተጠቃሚ ስለመሆናቸው መገለጫ እያቀረቡ በሌላ በኩል ይህንኑ ምስክርነታቸውን፣ ውዳሴያቸውን እና ማረጋገጫቸውን  እየካዱ እና እየቀላቀሉ ማምታታታቸው ስውር ዓላማቸውን ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡ ነገር ግን ህገመንግስቱ በሰጠን እውቅናና በመንግስት ድጋፍ የተሰሩ በርካታ መስጂዶችን “ጋዜጠኛ” ሁሴን ሲመቸው አድንቆ አጽንቶ  ወደዊኪሊክስ መረጃ ሲያመራ በአሜሪካ መንግስት እየታደሱና እየተጠበቁ የሚገኙ መስኪዶችን “የበሰበሱ የቆሻሻ ማከማቻ” ናቸው ሲል መግለፁ የበላበትን ወጪት ከመርገጡም ባሻገር ለእምነቱ ያለውን ንቀት የሚያጋልጥ ሲሆን፤ በዋናነት ግን ሁሴን ከድር የሙስሊም ስም መያዙን ብቻ እንደጥሩ አጋጣሚ የተጠቀመ የቀድሞው ቅንጅት ስብርባሪ መሆኑንና የደርጉ ስርዓት የሳንሱር ኦፊሰር የነበረ መሆኑን ያረጋጠልን  መጣጥፍ ነው፡፡